# ማነው ተጠያቂው?

*ስለ ጎሊናችን፣ ስለ እውነት ክብር*
*ሰው - ስለ ሰው ብሎ፣ እስቲ ሰው ይመስክር፤*
*በዚች ዓለምችን፣ መለኪያው ምንድን ነው*
*ከገዠና ተገዠ፣ ተጠያቂው ማነው...... ?*

ጥቂቶች በቡድን፣ ብዙሀኑን ገፍተው
የሰውን ስብዕና፣ ማንነቱን ገፈው፤
በጥይትም ይሁን፣ በታንክ ደፍጥጠው
እነሱ እንዲገዙ... ማነው የፈቀደው?

*ስለ ህሊናችን፣ እስቲ እንጠያየቅ*
*ሰው - ለራሱ ብሎ፣ ራሱን ይጠይቅ።*

ብዙ በልተው - ብዙ ‘ለማበት’
ብዙ ተግተው - ብዙ ለመሸናት፤
ለጮማ .... . ቅርናታቸው.........
ለውስኪ .... . ቅርሻታቸው.........
ለእኩይ .... . ምግባራቸው፤.........
እንደ አንድ ሰው ሆነው፣ ሲቆሙ በአንድነት
ለክቡር አላማ፣ ሌላው ሲሆን ‘ ‘ኩበት’ ’ ፤
እነሱ ምን ያ’ርጉት? . . . ምንስ ያቅርቡለት......?
ሰው ነኝ የሚል ዜጋ፣ ከተነዳ እንደ ከብት።

*ስለ ጎሊናችን፣ ስለ እውነት ክብር*
*ሰው - ስለ ሰው ብሎ፣ እስቲ ሰው ይናገር፤*
*በዚች ዓለምችን፣ መለኪያው ምንድን ነው*
*ከገዠና ተገዠ፣ ተጠያቂው ማነው......?*

ሀገርን አፍርሰው፣ ትውልደን አጥፊተው
እንድ ቅርጫ ስጋ፣ ህዝብንም ከፋፍለው
እጃቸውን በደም፣ በህዝብ አምባ ታጥበው፤
‘ ‘ ታላቁ ፍጡር፣ የዘመኑ ጀግና፣ ክቡር . . . " ከተባሉ
ገዥዎች ምን ያርጉ...?፣ ለምን አይፏልሉ...?
‘ ‘ ለምን እድሜ በቃህ’ ’ ፣ እንገዛለን አይሉ...?

*ስለ እውነት - በእውነት፣ እስቲ እንጠያየቅ*
*ሰው - ለራሱ ብሎ፣ ራሱን ይጠይቅ።*

የኪነ - ጥበብ ሰው፣ ምሁር ነኝ እያለ
ማንነቱን ከዶ፣ ሞያውን አርክሶ፣ በከርሱ እየማለ፤
"ሳይጠሩት - አቤት . . . . . . . ! "
"ሳይልኩት - ወዴት . . . . . . ! "

EthioLion.Com

''ጭራውን ከቆላ''፣ ከግራቸው ስር ልሁን፣ ልነጠፍ እያለ
ለገዢዎች እድሜ ፣ ሱባኤ ካደረ፣ ሰበካ ከዋለ፤
ማነው ተጠያቂው? . . . . በማን ላይ ይፈረድ?
መሪ በለሌበት፣ ፍትህ አይወለድ።።

*ስለ እውነት - በእውነት ፣ እስቲ እንጠያየቅ*
*ሰው - ለራሱ ብሎ፣ ራሱን ይጠይቅ።*

እየተራብ . . . . . . እያጠገባቸው
እየደህየ . . . . . . እያከበራቸው፤
እየታረዘ . . . . . . . እያስጌጥቸው
እያዋረዱት . . . . . . እየተዋረደላቸው፤
እየዘረፉት . . . . . . እያሞካሻቸው
እየገደሉት . . . . . . እያኖራቸው፤
በስሙ - በሀብቱ፣ ሲደለልበት
እንደ እቃ ሲቆጠር፣ ሲነገድበት፤
''ዜጋ'' ነኝ ሲላቸው፣ እየሳቁበት
የ'ኔ እሚለው ሀገር፣ እምነት ሲያሳጡት፤...... .
"አደናቅፎኝ ነው፣ የእናቴ መቀነት......"
"ሆድ ይፍጀው..." እያለ፣ ከጠበቀ ምፅ'ት፤
ገዥዎች ምን ያርጉ? . . . . ምን ይፈይዱለት?
ለመምራት አይደለም፣ ወይም ለመመራት
ለመግዛት እኮ ነው፣ "ገዳይ. . . ." ነን ያሉት።

*ስለ ኅሊናችን ፣ ስለ እውነት ክብር*
*ሰው - ስለ ሰው ብሎ፣ እስቲ ሰው ይናገር፤*
*በዚች ዓለምችን፣ መለኪያው ምንድን ነው*
*ከገዥና ተገዥ፣ ተጠያቂው ማነው.........?*

-------//-------

ፊልጶስ / 2003
ለአስተያየት:e-mail: hol-land@hotmail.com